# ኒዎሊበራሊዝም እና ጥገኛው ቡድን

(ክፍል አንድ)

ዮናስ 09-24-14

የዚህ ጽሁፍ መነሻ በሰብዓዊ መብት ስም የሚንቀሳቀሡ ኒዮ ሊበራል ሃይሎች ኢትዮጵያን በተመለከተ ሁል ጊዜ የሚያወጧቸው ሠብዓዊ መብትን የተመለከቱ ሪፖርቶች በትዝታና ቁዘማ ውስጥ ሆነው በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ ከሚናውዙ ተቃዋሚዎች ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለተኛው ገጽታ መሆናቸውን ማመላከት፣ መጨረሻቸውም ክሽፈት መሆኑን ማሳየት ነው።

በኢትዮጵያ መንግስት በኩል በተደጋጋሚ እንደሚገለፀው እነዚህ በሠብአዊ መብት ስም የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ጉዳያቸው የርዕዮተ ዓለም እንጂ የሠብዓዊ መብት አይደለም፤ ለዚህም በርከት ያሉ ማሣያዎች ሲቀርቡ ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና በነፃ ፕሬስ ስም የሚንቀሣቀሡ ኃይሎች የእነዚህንና ሠብዓዊ መብትን የተመለከቱ ሪፖርቶችን የሚያወጡ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን ትክክለኛና መረጃን መሠረት ያደረጉ ናቸው ሲሉ በማወደስ ብቻ ሳያበቁ ስርአት ለመገርሰስ የእገዛ ጥሪ ሲያቀርቡላቸው በተደጋጋሚ ማስተዋል ችለናል፡፡ ሆኖም ግን በተጨባጭ የሚታዩትና የሚስተዋሉት በዓለማችን የሚገኙ በተለይም በምዕራባውያኑ የሚመሩ የሠብአዊ መብት ተሚጋች ነን የሚሉ ድርጅቶች ትክክለኛውን አሠራርና ሥነ ምግባር ተከትለው ሳይሆን የሚሠሩት የእነርሡን አይዲዮሎጂና ርዕዮተ ዓለም አልጋትም ያለውን ሁሉ በመፈረጅ ተላላኪዎቻቸውን ስልጣን ላይ ማንበር ነው።

የእነዚህ ሃይሎች በቀቀን የሆኑ የሃገር ውስጥ ጽንፈኛ ሃይሎች "የእነዚህ ድርጅቶች ሪፖርት በመረጃ የተደገፈና ሙያዊ አሠራርን የተከተለ ነው" ሲሉ አይናቸውን በጨው አጥበው ይከራከራሉ፡፡ በመከራከር ብቻም ሳያቆሙ በሁለት እግራቸው መቆም ባልቻሉበት ሁኔታ እራሳቸውን በዴሞክራትነት እያንቆለጳጰሱ ገዢ ስርአቱን በማጣጣልም ያብራሉ። ለመሆኑ የትኛው የሠብዓዊ መብት ተሚጋች ነው አሜሪካ በኢራቅ ላይ አዋጅ ስታስነግር 'ኧረ ተይ' ለማለት የደፈረው? ኧረ የትኛውስ የሰብዓዊ መብት ጠባቂ ነው አሜሪካ መሠስ

ብላ አፍጋኒስታን ስትገባና ስትወጣ ‘ኧረ በህግ’ ያላት፤ ኧረ የትኛውስ ደፋር የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነው በጓንታናሞ የሚሠቃዩትን ሰዎች ‘ይብቃቸው’ ሲል አንድ አረፍተነገር የፃፈ፤ ምነው እሥራኤል እንዳሻት ስታፈነዳና ስታጨሠው አንድ መስመር ሪፖርት ተመልክተን የምናውቀው፤ አዎ ሰምተንና ተመልክተን የማናውቀው ጉዳያቸው ሰብአዊ መብት ሳይሆን ከቆዛሚው ተቃዋሚ ጋር በማበር የቀለም አብዮትን ማቀጣጠል አልያም ምርጫን በማጣጣል ለአሸናፊ ፓርቲ እውቅና መንፈግ ነው።

ያለፈውን አመት የአምነስቲ አመታዊ ሪፖር ለአብነት እዚህ ጋር እናስታውስ፤ በቦስተኑ ፍንዳታ ያለ አግባብ ሠብአዊ መብቱ በይፋ ሲገፈፍና ሲንገላታ የነበረውን የወቅቱ ጉዳይ ሊያውም እዛው በቅርቡ እያለለት ዝም ያለው አምነስቲ ስለጋምቤላ ያወራው የሰብአዊ መብት ጉዳይ አሳስቦት እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሙስና እንቶ ፈንቶ ምክንያቶች የሚሞግቱቱ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነን ባዮች ምነውሣ ተመጣጣኝ ያልሆነና እጅግ አስከፊ የቅጣት እርምጃ ነው የምንወስደው ሲሉና የአሜሪካ ባለስልጣናት በይፋ ሲደግፉ አምነስቲ ዝምታን መምረጡም የሚያረጋግጥልን ሰብአዊ መብት ስሙ እንጂ ግብሩ የቀለም አብዮት መሆኑን ነው። ከአምነስቲ የባሱብንና ስንመክራቸው ያፌዙብን የተሠናከለ አንዳች የልማትም ሆነ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሌለበት ሃገር ላይ የተቀመጡትና የእነዚሁ ሃይሎች በቀቀን የሆኑቱ ናቸው፤ ያም ሆኖ ግን እንደተናገርነው የጊዜ ጉዳይ ነበርና ሁሉም በየጥጋ ጥጉ ፎርሾበት እርስ በርሱ እየተተጋተገ ነው፡፡ ወደ መንደር ማሰባሰቡም ስንመጣ የምናገኘው ተመሳሳይ ነው፤ ዘርፉ ተቃዋሚዎችና ስመ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሚጋመዱበት ቀጭን ገመድ ነው፡፡

በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታን እና ነዳጄን በራሜ አማራጭ፣ በራሜ ፈቃድ በሚሉ የመካከለኛው ምሥራቅ ዜጎች ላይ የሚደርሥ አፈናና የሚዘንብ ጥይት ለምን ብሎ የጠየቀ የሠብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ የሚል አካል አለመኖሩን አስቀድመን በተናገርነው መሰረት ይኸው ቀኑ ደረሰና በሁሉም ቤት በተነሳው እሳት ሲረጋገጥ ለማስታመም እንኳ ብቅ ያለ ስመ ሰብአዊ መብት አለመኖሩ በባዶ ትዝታና ቁዘማ ሲማስኑ እንደነበር አረጋግጧል፡፡ የሠፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንት በመንደር ማሠባሠብ ሥራዎችን በተመለከተ ተቆርቋሪ ነን በማለት የተቀናጀ ሪፖርት የሚወረውሩት እነዚህ ሃይች ለውጭ ሃገር ኩባንያዎች መሬቱን ለመሸጥ ነው ሲሉ ኢትዮጵያን ቢከሡም በአንፃሩ እነርሡ ልቀቁ ከተባሉትና በሃይል ከያዙት የዙምባብዌ መሬት እንዴት ባለ ሁናቴ እንደለቀቁና በሃይል የያዙትን መሬት ለምን

ተነጠቅን ብለው ዙምባብዌን እስከዛሬ የበቀል ፅዋን እያስጎነጪት መሆናቸውን የማናውቅ ይመስል ደርሠው መሬቱን ለውጭ ዜጎች ሊሸጡ ነው ብለው ከተቃዋሚዎቹ ጋር ሙሾ የመውረዳቸውም ሚስጥር የከሰረ ፖለቲካ ነው፡፡

ምን ይህ ብቻ ስለ ራሣችን የምናውቀውና ማወቅ የሚገባን እኛ እንደመሆናችን አውቅላችኋለሁ ካላወቅንላችሁ የማለትን እና መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ስም በስለላ ሥራ ላይ ተሠማርተው ለተገኙትና ሉዓላዊነታችንን በመድፈር ሥራ ላይ በዘመቻ ተሠማርተውና በነርሡ ጥገኝነት ሥር ለዘላለም እንድንቆይ ሲሠሩ ለነበሩ ሃይሎች አብረን የምንቆየው በመተጋገዝ ላይ በተመሠረተ የልማት አቅጣጫ ላይ እንጂ በእነርሡም አገር እንደ ሆነው ሁሉ በውስጥ ጉዳያችን ገብታችሁ አይሆንም የሚል ሕግ አበጅተን ተግባራዊ ማድረጋችን የሚያንጫጫቸው የውጭ ሃይሎች ገብተው ባለመፈትፈታቸውና ርዕዮተ ዓለማቸውን ሊግቱን ባለመቻላቸው መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በውስጥ ጉዳያችን ካልገባሁ የሚልና ልማታችን ላይ ሰንካላ በመሆን እድሜ ለዘላለም የእነርሡ ጥገኛ እንድንሆን  የሚሻ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት  ከሽባነትም በላይ እንክትክቱ ይወጣ ዘንድ መስራት የሁላችንም ሃላፊነት እንጂ የማንም ሊሆን እንደማይገባ ስንመክር እምቢኝ ያሉት ሁሉ ይኸው በመሪዎቻቸው አምባገነንነት እና በውስጠ ዴሞክራሲያዊ እጦት ሲሻቸው በጡጫ ሲሻቸው ደግሞ በፌስ ቡክ እየተለጣለጡ ነው።

ከሽብርተኝነት ህጉ ጋር ተያይዞም የሚነሣው በተመሣሣይ ነው፡፡ ስለሠላማችን ከእኛ በላይ ማንም ሊያገባው እንደማይገባው ሁሉ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ስም አልሆን ሲል በሌላም አቅጣጫ ሊመጣ እንደሚችል በመገመትና ህዝቦች በሠላም፣ በነፃነትና በተረጋጋ ሁኔታ ለመኖር ያላቸው መብት ከሽብርተኝነት አደጋ ሁል ጊዜ መጠበቅ ያለበት መሆኑ፣ ሽብርተኝነት ለሃገራችን ሠላም፣ ደህንነትና እድገት ፀር እንደሆነ ለአካባቢያችንና ለዓለም ሠላም እና ደህንነትም ከፍተኛ ሥጋት እንደሆነ ግንዛቤ የተወሠደ መሆኑ፤ በሥራ ላይ ያሉት የሃገሪቱ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የህግ አቅም መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የፀረ ሽብርተኝነቱን ሕግ ማውጣት አንድ ሃላፊነት ከሚሠማውና በህዝብ ከተመረጠ  መንግስት የሚጠበቅና በዚሁ ተግባር ላይ የተሠማሩትን እና ሊሠማሩ ያቆበቆቡትን በህግ አግባብ መሠረት መቅጣቱ ያለምንም የሕግ አግባብና ተጨማሪ ህግጋት ኮሽ ባለበት ላይ ሁሉ ቦንብ ማዝነብ ከለመዱት ሃገሮች ክስ ቢመጣብን እዛው በፀበላችሁ ብለን ከማለፍ ውጪ አማራጭ የሌለን

መሆኑና ከተያያዝነው ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መዘናጋት እንደማንችል አስቀድመን እቅጩን ነግረናል ፡፡

የትኛውንም አይነት የዴሞክራሲ ሥርዓት በሚከተሉ ሃገራትም ሆነ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጽንሠ ሃሳብ መሠረት ከምርጫ ውጪ የሚደረግ የስልጣን ዘመቻ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ለድርድር የማይቀርብ እውነታ ነው፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አባት ነን የሚሉትና አባትነታቸው በተደጋጋሚ የሚነገርላቸው አሜሪካና ምዕራባውያን ሃገራትም ይህንኑ ጉዳይ በተደጋጋሚ የሚያሠምሩበትና አጽንኦት የሚሠጡት ጉዳይ ቢሆንም ለእነርሱ አክራሪ የገበያ ሥርዓት ያልተመቹ ሃገራትን ግን ከሃገራቱ ህዝብ ፈቃድና ህገመንግስት  ውጪ ሥርዓት ለመለወጥና መንግስት ለመገልበጥ የተለያዩ ሙከራዎችን ማድረጋቸውና፣ ከላይ በተገለጸው  አግባብ እኛ ጋር በተደጋጋሚ ተሞክሮ ቢከሽፍም በሚበዙ ሃገራት ግን ይኸው በዴሞክራሲ ስም የፈጠሩት ሤራ ስኬታማ እንዳደረጋቸው በርከት ያሉ የአፍሪካ ሃገራትን የምርጫ ትርምሶችና ያለምርጫ የሚከናወኑ አብዮቶችን እና ትተው ያለፉትን ዳፋ በማስታወስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው እነዚህ የገበያ አክራሪ ሃይሎች የእነሡን መሻት ያልፈቀደን ሃገር እንዳሻቸው አናውጠው ሥርኣት ሊለውጡ የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ሁሉ ዴሞክራሲያዊ የሚመስሉ እና ስለ ዴሞክራሲ በሚዘምሩ ተቋማትና ግለሠቦች አማካኝነት መሆኑም ከላይ የተገለጸና የትርክታችን አብይ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የሠብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ በየሃገራቱ ያሉ አኩራፊና  ኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲከኞች እንዲሁም ፍርፋሪ ለቃቃሚ የሆኑ ፕሬሶችን ከኒዮሊበራል ሚዲያው ጋር ተመጋግበው እንዲሠሩ ማድረግ ዋነኛ ስልታቸው መሆኑም እንዲሁ ጠሰ የደረሰባቸውና ሙከራውን ያከሸፉ ሃገራትን እንዲሁም በባዶ ቀርተው ከሰሞኑ የሚተራመሱ የሃገሬ ፓርቲዎችን በማስታወስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሃገራችን በምትከተለው የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሚከተሉ ሃገራት እንደሚደረገው ሁሉ ሃሣብን በነፃ የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ የመሠብሠብ እንዲሁም ሠላማዊ ሠልፎችን የማድረግ መብት የተፈቀደና ህገመንግስታዊ ዋስትናም የተሰጠው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ግን ደግሞ ሃሣብን በነፃነት በመግለጽ መብት ሽፋን፣ በመሠብሠብና በመደራጀት መብት ስም፣ በሠላማዊ ሰልፍ ጥላ በመከለል የሚደረግ ማንኛውንም ዓይነት ህገወጥ እንቅስቃሴ የመመከትና በህግ አግባብ እርምጃ የመውሰድ መብት እንዲሁ በስልጣን ላይ ለሚገኘው መንግስት የተሠጠ ሃላፊነትና ይኸውም ሃላፊነት በህገመንግስቱ የተረጋገጠ መሆኑም ላይ ታሠምሩልኝ ዘንዳ እሻለሁ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው፣ ከምርጫ ውጭ የሚደረጉ የሥልጣን መያዣ መንገዶች በተለይም የቀለም አብዮት የሚከናወነው በውጭ በሚገኙ አክራሪ ሃይሎች፣ አክራሪ ዲያስፖራዎች እና በሃገር ውስጥ በሚገኙ የከሠሩ ፖለቲከኞች፣ ፓርቲዎቻቸውና ፍርፋሪ ለቃቃሚ በሆኑ ፕሬሦች መሆኑም በተግባር የታየ እውነታ ነው፡፡ በአንድ አገር ውስጥ የቀለም አብዮት እንዲኖርና አልፎ ተርፎም እንዲሳካ ከማድረግ አኳያ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ጠንካራ አንድነት ያለው የተቃዋሚ ጎራ መኖር እንዳለበት በመስኩ የተራቀቁት የቀለም አብዮተኞች ይገልፃሉ፡፡ በአገራችንም በ97 ዓ.ም ተሞክሮ የከሸፈው የቀለም አብዮት የተለያዩ ነገር ግን ከሞላ ጎደል በአንድ ተመሳሳይ የቀለም አብዮት ስትራተጂ የሚመሩ ተቃዋሚ ድርጅቶች የመሩትና እንደየአቅማቸው የተወኑበት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ጀምሮት በሂደት ቅንጅት ከተፈጠረ በኋላ መሪነቱን የተቆጣጠረው የ97ቱ የከሸፈ ሙከራ ከሞላ ጎደል በሁሉም ተቃዋሚዎች የታመነበትና የተደገፈ የቀለም አብዮት ነበር፡፡

በአገራችን የሚገኘው የተቃውሞ ጎራ (ምንም እንኳን ባነገበው አላማና በኪራይ ሰብሳቢ ባህሪው አንድ ቢሆንም) ከምርጫ 97 በኋላ የአገሪቱን ህጎች አክብሮ ለመታገል ዝግጁ በመሆንና ባለመሆን መካከል ልዩነቶች እያሳየ መሆኑ ይኸው በ10ኛ አመቱም በተመሳሳይ እየደገመውና እያየን ነው፡፡ የራሳቸውን የቤት ስራ መጨረስ ተስኗቸው እየታመሱ ከሚገኙት ሰማያዊ፣ አንድነት፣ መድረክ እና መኢአድ ባሻገር የሚገኙ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን ሂደቱን የሚያጥላላ ዘመቻ ከማድረግ አኳያ ያልተሻገሩት መሰረታዊ ገደብ ያለባቸው ቢሆንም ደፍረው የፀረ ህገ-መንግስት ቅስቀሳና የአመፅ ጥሪ ማካሄድ ውስጥ ባለመግባት ከፅንፈኛው የተቃዋሚ ጎራ የተለየ አካሄድ መከተል እንደሚፈልጉ

ማመላከታቸው ሊዘነጋ ባይገባም፤ ይህ አዝማሚያ በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ ሂደት የአመፅ ሃይሎች  በሚወስዱት ፅኑ አቋም ወይም መዋለል የሚፈተን መሆኑም ሊረሳ አይገባም።

ይህ ፅንፈኛ የሆነው የተቃዋሚ ክፍል ከ97ቱ እና ከ2002ቱ ስህተት ካለመማሩም በላይ በስህተቱ ትዝታ እየቆዘመና የለየለት ኪራይ ሰብሳቢ ፍላጎቱን ለማሳካት አመፅን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚሻ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን በራሱ በቤቱ የፈጥኝ ተይዞ እየማቀቀና ወደመቃብሩ እየወረደ መሆኑን ሰሞንኛዎቹን የነሰማያዊ፣ አንድነትና መኢአድ በማስተዋል ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ችግር በሌለበት ችግር የተፈጠረ አስመስሎ ሰፊ የፈጠራ መረጃ ያቀርብ የነበረው ቆዛሚ እውነተኛው ችግር በቤቱ ገብቶበት እየቆላው ነው፡፡ ዴሞክራሲያችን ለጋ ከመሆኑ በመነሳት ዴሞክራሲያዊ ስርአቱን ለመገንባት    ከሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ሾልከው የሚፈፀሙ የስነ-ምግባር ጥሰቶችን አጋኖና አባዝቶ በማቅረብ ህዝቡ በስርአቱ ላይ አመኔታ እንዲያጣ ለማድረግ ሌት ተቀን ሲፍጨረጨር የነበረው ሃይል በስነ ምግባር ድርቅ ክፉኛ ተመቶ እየተዘላለፈ ነው፡፡ በገዢው ፓርቲና በመንግስት በኩል ስህተት ከታጣም በአንድ በኩል ሆን ብሎ ህግ በመጣስ በመድበለ ፓርቲ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደቱ ላይ ፈተና እየደቀነ መንግሥት ህግ ለማስከበር ሲንቀሳቀስ ምህዳር ጠበበ እያለ ሲያራግብ እንዳልነበር፣ በራሱ ቤት ምህዳሩ ጠቦ መፈናፈኛ ማጣቱን እየነገረንና በዚህም መነሻ አንጃ ፈጥሮ እየተተጋተገ መሆኑን፣ ጡጫው የበረታባቸውም በይፋ መሰናበታቸውን እያየን ነው፤ በሌላ በኩል መንግስት ዴሞክራሲያዊ ምህዳሩ ጠቧል የሚል ወቀሳ እንዳይቀርብ በመስጋት የህግ ጥሰትን አይቶ እንዳላየ ሲያልፍ ደግሞ ህግ የመጣስ መንፈስ እንዲበራከትና ወደ አመፅ ለመንደርደር የሚያመች ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል እንቅስቃሴ እንዳካሄዱቱ ሁሉ በቤታቸው ህግ ጠፍቶ እተናቆሩ መሆኑም የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ የቀለም አብዮት ሃይሎች ጋር በፈጠሩት ተመጋባቢ ግንኙነት ስርአቱን ጥላሸት የመቀባት ሰፊ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻን እንዳካሄዱቱ ሁሉ በተራቸው እውነተኛውን ጥላሸት እርስ በርስ እየተቀባበሉ ነው፡፡

በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎችን እንደ አባሎቻቸው በማቅረብ ግፍ የተፈፀመ አስመስሎ ማቅረብ፣ በደረቅ ወንጀል የታሰሩ ሰዎችን ስም ለቃቅሞ በፖለቲካ የታሰሩ አስመስሎ ተደጋጋሚ የፕሬስ መግለጫ ማውጣት፣ በሚዲያ በሚካሄዱ

ውይይቶችና በፕሬስ ውጤቶች በአምደኝነት ስም የሚለቋቸው ፅሁፎች ላይ ህግ የማይፈቅዳቸው የቋንቋ አጠቃቀሞችን ደጋግሞ ማውጣትና በመጨረሻም ይህ ሲከለከል *የመጻፍ መብታችን ተጣሰ* ብሎ ዘመቻ መክፈት የለት ተለት ስራው የነበረው ይህ አፍቃሬ ኒዎሊብራል ሃይል ዛሬ እራሱ ላይ ተግባራዊ እያደረገውና ብለን ነበር ብለን እንድንዘባበት ያስቻለን ሃቅ ነው፡፡

እነርሱ መስማት ባይፈልጉምና ዛሬ ደርሶባቸው ቢያዩትም ጃስ ሲላቸው የነበረው የኒዮ ሊበራሉ አክራሪ ሃይል ከራሱ መጽሃፍ በስተቀር ሌላ እንዳይነበብና *መመሪያ* እንዲሆን የማይፈልግ፣ የራሱን *መመሪያ* በሌሎች ላይ በውድም በግድም መጫን የሚፈልግ መሆኑን ዛሬም ደግመን ልንናገር ግድ ይለናል፡፡

ይህ አክራሪ ሃይል ዓለምን በራሱ አምሳል ለመቅረጽና ለእርሱ ብቻ የምትመች እንድትሆን ለማድረግ ሁሉንም ዓይነት ማስገደጃ *መሣሪያዎች* መጠቀም የለመደ ነው፡፡ የማስገደጃ *መሣሪያ* ከመጠቀሙ በፊት በማባበል ከተሣካለት በዚሁ ተማምኖ የበላይነቱን ያረጋግጣል፡፡ ይህ አልሠራ ካለው ደግሞ ሃይልን ከዚህም አልፎ የቀለም አብዮትን እንደዋነኛ ማስፈፀሚያ የሚጠቀምበት መሆኑ በተግባር ታይቷል፡፡ ከላይ የተጠቀሠውና በ97 እና 2002 ምርጫ ዋዜማና ማግስት በሃገራችን ላይ ተሞክሮ የከሸፈው የቀለም አብዮትም ሃገራችን የራሷን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ በመከተሏና *በአክራሪው ሃይል መመሪያ አልመራም፣ የራሄንም ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እገነባለሁ እንጂ የአክራሪ ሃይሉን መነባንብ መዋጥ ሲያልፍም አይነካካኝ* በማለቷ መሆኑን ያስታውሷል፡፡

በምርጫ 97 እና 2002 ከእነዚህ አክራሪ ሃይሎች በኩል ሲቀጣጠል የነበረው እና በተበታተነ ነገር ግን በእሩምታ መልክ ሲተኮስ የነበረው ጥይት ከነሂውማን ራይትስ ዎች፣ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሲፒጄ (የጋዜጠኞች መብት አስጠባቂ ነኝ ባይ ድርጅት) ወዘተ . . . እንደነበርም አይዘነጋም፡፡ ቆዛሚዎቹ በራሳቸው ጊዜ ወደመቃብሩ እያመሩ ሆነ እንጂ ለምርጫ 2007 ታስቦ የነበረው ተኩስም በመሬት ቅርምትና በነጻ ፕሬስ እንዲሁም በጸረ ሽብርተኝነቱ አዋጅና በመያዶች ህግ አስባብ እየተቀባበለ የሚገኘው እነዚሁ አክራሪ ሃይሎች በሚመሩት የያንጊዜዎቹ ተቋማት እና በ97 ትዝታ ሲናጡ በነበሩት ተቃዋሚዎች ጥምረት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

ስለሆነም ጋብቻ የፈፀሙት  የሃገሬ ተቃዋሚ ሃይሎችና  የቀለም አብዮት አራማጆች እንደሚሉትና በእነርሡ ቅጥረኝነት የቀለም አብዮት በኢትዮጵያ እጃቸውን አስገብተው ለመፈትፈት የሚያስችላቸው  የዴሞክራሲ እጦት ስላለ አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ባለፉት 22 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ተገንብቷልና፡፡ ጉዳዩ የሰብዓዊ መብት የማስከበር የቀሠቀሠውም አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ሳትጠብቅ በህቦቿ ትግል ሠብአዊ መብትን  አስከብራለችና ነው፡፡ ጉዳዩ የነፃ ገበያም አይደለም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ስፋትና ፍጥነት የነፃ ገበያ ስርዓቱ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ ዋነኛ አንቀሣቃሽ የሆነው የግል  ሴክተር በልማታዊ አቅጣጫ እየተፈጠረና እየተመነደገ ነውና፡፡ ስለሆነም በቀለም አብዮተኞች ጣልቃ ገብነት  ይህን ሂደት የፈጠረውና ያስቀጠለው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይል አገሪቱን ይምራት? ወይስ እነርሡ እንደልባቸው የሚያሽከረክሩት ተላላኪ ኪራይ ሰብሳቢ ሃይል ሥልጣኑን ይይዛል? የሚለው የነበረ ቢሆንም እርሱም የተላላኪዎቹን  ቤት በወረረው የጸረ ዴሞክራሲያዊነት ወረርሽኝ እንዳያንሰራራ ሆኖ ቆሌ እርቆታል፡፡

በሃይማኖት ስም ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳዎችን ማራገቡ አሁንም የቀጠለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከፕሬስ ነፃነት ጋር በማያያዝ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን የማጣጣል ዘመቻውም እየተገፋበት የመሆኑም ነገር ሳይዘነጋ፣ በእነዚሁ የገበያ አክራሪና የቀለም አብዮት አባት በሚባሉ ሃገራት በጀት የሚተዳደሩ ሚዲያዎች የፕሬስ ነፃነትንና የሰብአዊ መብት አያያዝን ጉዳይ በማጣመም ሠፊ ሽፋን እየሰጡ የመሆናቸው ነገር  ለምርጫ 2007 የሚደረገውን የቀለም አብዮት ዝግጅት ከወዲሁ እንዲሸተን አስችሎን የነበር ቢሆንም ካምፑ ከሽታም በዘለለ ተግባራዊ የቀለም አብዮት ተመቶ ለህክምናም እንዳይመች ሆኖ ተኝቷል፡፡

ባጠቃላይ፣ በምርጫ ዋዜማ ላይ የምህዳርና የፕሬስ ጉዳይን በማንሳት ህዝብና መንግስትን አለያይቶ የገበያ አክራሪነት ፍልስፍናን ሳያላምጡ ለሚውጡ ሃይሎች የመንግስትን ስልጣን

በአቋራጭ ለመለገስ ሲሰራ የምናውቀውና ከላይ በተመለከተው አግባብ የቀለም አብዮትን አጀንዳ በማቃለጥ ተግባሩ በምርጫ 97ትም ሆነ 2002 ላይ የምናስታውሰው የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ዛሬም  በ2007 የምርጫ ዋዜማ ላይ ይህንኑ ሥራ ሊገፋበት የቋምጦ ቢሆንም አጫፋሪዎቹ ተኘተዋልና እንዳማረው ቀርቷል፣ ይቀራልም፡፡